Date: Aug 18, 2013

የጽሞና ጽሁፍ ክፍል አንድ (Devotional article one)

የጸሎት ጥልቀት(ተግባራዊ እርምጃ)

ረዘም ያለ ጸሎትን ስናስብ ምንም ብዙ ጊዜ በስጋ ብንጀምርም በመንፈስ እንደምንጨርስ በመተማመንና በጸሎታችንም ድንቅ ነገርን እንደምናይ ተስፋ በማድረግ በጌታ ፊት እንወደቅ፡፡ቶሎ እንድናቋርጥ እና ወደ ሌሎች ጉዳዮች እንድንሄድ ወደ ነፍሳችን ግብዣዎች ይመጣሉና እነዚህን መንፈስን የሚያረጋጉ መልእክቶች ወደ ጎን በማድረግና በመጨከን በጸሎት እንገስግስ፡፡

ስለ ጸሎት ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ጸሎት ከሶስት በላይ እርከኖች (dimensions)እንዳሉት ይናገራሉ፡፡እነርሱም፡ -

1.የውጨኛው አደባባይ(the outer court)

2.ቅድስት/መሀከለኛው አደባባይ(holy/the middle court)

3.ውስጠኛው አደባባይ/ቅድስተ ቅዱሳን(holy of holies)

ብዙዎቻችን በጸሎት ጊዜያችን የውጨኛውን አደባባይ ተሳልመንና የጌታን ጸጋ ሳንካፈልና በረከቱን ሳናይ ነው የምናቋርጠው ምንም እንኳ ዲሲፕሊን እንደሚያስፈልገን ብናምንም፡ለዚህ መፍትሄው ጽኑ የሆነ ውሳኔና መጨከን ነው፡፡ደጋግመን ስናደርገው ትግል መሆኑም ይቀራል፡፡

እነዚህ የጸሎት እርከኖች(dimensions) ሉቃስ 11፡9 ላይ በሚገባን ሁኔታ ተቀምጠዋል፡፡እነርሱም ፡-

1.መጠየቅ (the asking realm)፡የመጀመሪያና ብዙ ትግል የሌለው በአእምሮአችን የምንጸልየው ጸሎት

2.ፊቱን መፈለግ(the seeking realm)፡በመጠኑም ቢሆን ጠንከር ያለና መንፈሱ እስኪሰማን(recognize) ድረስ የምንጸልየው ጸሎት ነው

3.ማንኳኳት(the knocking realm)፡በጣም የጠለቀ እና በመንፈስ የሚጸለይ ጸሎት እና ብዙ ጊዜ ዝምታ የሚበዛው ጸሎት ነው

እንዳውም ይኸው ቃል ወረድ ብሎ ቀጥር 10 ላይ እንደ ተስፋ ቃል ሆኖ ተቀምጧል፡፡እንዲህ ይነበባል፡- <<የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤የሚፈልግም ያገኛል፤መዝጊያን ለሚያንኳኳውም ይከፈትለታል፡፡ >> የሚገርም የተስፋ ቃል ነው በሕይወቴም ሲሰራ ስላየሁት ያስደንቀኛል፡፡ስለዚህ የእግዚአብሄር መንፈስ እንደሚመራን ሆነን ድምጹን እየሰማን፣ እየታዘዘንና እጃችንን ይዞ እንዲመራን ከፈቀደልንለትና እርግት ብለን በቂ ገዜ በፊቱ ብንሆን ግሩም ጊዜዎችን እናሳልፋለን ህብረታችንም ይጠልቃል፡፡ባጭሩ ልንወስድ የሚገባን ተግባራዊ እርምጃዎች(የራሴን ልምድ ላካፍላችሁ እናንተ ከኔ የተሻሉ መንገዶች ሊኖሯችሁ ይችላል)፡-

- ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነት ጸሎቶችን እንዳንጸልይና የእግዚአብሄርን ሙሉ በረከት እንዳንቀበል የሚያረገን የጠላት ተጽእኖ ሊሆን ይችላል፡፡ስለዚህ በመንፈስ በመለየት በሀይል እየተቃወምነም መጸለይ አለብን፡፡

- በተጨማሪም የጸሎትና የአምልኮ መዝሙሮችን ከፍተን መንፈሳችን እንዲነቃቃና እንዲቀጣጠል ብናደርግ ጥሩ ነው፡፡
- ሌላው በመሀል መጽሀፍ ቅዱስ ወስጥ ከምንጸልይባቸው ሁኔታዎች ጋር የሚሄዱ ቃሎችን በማንበብና በጸሎት መንፈስ ሆነን በማሰላሰል የበለጠ መንፈሳችንን ለቀጣይ ጸሎት ሊነሳሳ ይችላል፡፡
- አእምሮአችን እንዳይሰባሰብ የሚያደርጉ በግል የምናወቃቸውን ነገሮች በወሳኔ ከአካባቢያችን ማራቅ (ለምሳሌ ሞባይላችንን ማጥፋት)

ትልቁ ነገር ግን ወሳኔ ነው፡እኔ ቢሰማኝም ባይሰማኝም አልነሳም ከጸሎት ብዬ የምወስንባቸው ጊዜዎች አሉ፡እንዳውም እንዳልጸልይ በከበደኝ ጊዜ ገፍቼ ብዙ ሰኣት በወሳኔ ስጸልይ ካሰብሁት በላይ አስደናቂ ጊዜን አሳልፌ አውቃለሁ፡ተቁነጥንጠን ስንነሳ ያንኑ የምናወቀውን ህይወትና ኑሮ ነው የምንቀጥለው ከጌታ ጋር ብናሳልፍ ግን ህይወታችን እየተለወጠና የጌታ ጸጋ በሕይወታችን እያደገ ይመጣል፡፡አለበለዚያ ልንመኝ ልናስማስል እና ዝም ብሎ በባዶው ልንጓጓ እንችል ይሆናል እንጂ በነካ ነካ ጸሎት የእግዚአብሄርን ክብርና ጉብኝቱን አናይም፡ ስለዚህ ሚልካሜዙ እጁ በመካከላችን እንድትበዛ በጸሎት ማጋደል አለብን፡፡

ጸሎት ፡-ጌታ ሆይ ከዳር ዳር ጸሎት እባክህ ክብርህን ወደምናይበት ጥልቀት ወስጥ ክተተን!

የጽሞና ጽሁፍ ክፍል ሁለት (Devotional article two)

በመንፈስ መጸለይ(Praying in the spirit)

በጭንቀትና በሀዘን ወስጥ ወይም ግራ በሚገባ ሁኔታ ወስጥ ሆነን እንዴት እንደምንጸልይ አናወቅም፡አንዳንደም የምናወጣቸው ቃላቶች እና አእምሮአችን ልንጸልይ የምንፈልገውን መግለጽ ሊያቅታቸው ይችላል፡፡ቃላት ጸሎታችንን መግለጽ ሲያቅተው በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍ እርሱ በወስጣችን እንዲቃትት ብንፈቅድለት ከፍ ያለ ጸሎት መጸለይ እንችላለን፡፡ሮሜ፡26-27

ብዙ የስነ-መለኮት አዋቂዎች ሀና በመንፈስ ትጸልይ እንደነበረ ይስማማሉ፡፡(1ሳሙ1፡12-16)ከንፈሯ ይንቀሳቀስ ነበር ነገር ግን ድምጽዋ አይሰማም ነበር፡፡ስለዚህ ታላቁ የእግዚአብሄር ሰው ኤሊ ተሳስቶ ጠጥታ የሰከረች ማለው፡ሀና ከበድ ባለ ጭንቀት ወስጥ ስለ ነበረች በመንፈስ ትቃትት ነበር፡፡ሃና በአራቱም ማእዘን እየደረሰባት ካለው ፈተና የተነሳ ምሬት ወስጥ ነበረች፡፡በሴትነቷ እና በሚስትነት ማንነቷ ላይ የተነጣጠረ አደጋ ስለነበረ ነው መከራዋን ከበድ ያደረገው፡ስለዚህም እግዚአብሄርን በጽኑ ፈለገችው፡በመንፈስ ብርቱ ጸሎትን ጸለየች፡፡በዘመኑ ብርቱ የነበረ ሳሙኤልን ወለደች፡፡

እኛም አዳጋች ነገር ሲገጥመን ወደ ጸጋው ዙፋን መጥተን በመንፈስ ብንጸልይና ረዘም ላሉ ሰአታት ብንቃትት ጸሎቱ በቀጥታ ከእግዚአብሄር ጋር ስለሚያገናኘን እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ ያለ ጸሎትን እንጸልያለን፡፡ችግራችንም በእግዚአብሄር ጊዜ ይንከባለላል፡፡

እባክህ ጌታ ሆይ የጸሎትን ሚስጥር ግለጥልን!

(የጽሞና ጽሁፍ ክፍል ሶስት)Devotional article 3

የምጥ ጸሎት (travailing prayer)

የምጥ ጸሎት በተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ምሪቶችና መረዳቶች የሚከናወን ጸሎት ሲሆን ብዙ ጊዜ ከፊት ለፊት ተግዳሮቶች፣መከራዎች እና ልብን የሚሰብሩ ክስተቶች በህይወታችን ሲያልፉ ልንጸልየው እንችላለን፡፡

የምጥ ጸሎት ለ 5 ደቂቃ ብቻ ሊጸለይ ይችላል ወይም ረዘም ላሉ ቀናት ሊጸለይ ይችላል፡፡አብዛኛውን ጊዜ የጸሎት ሸክሙ መንፈሳችን ወስጥ እስካለ ድረስ አያሳርፈንም፡፡እኛም ማለቀቅ እስኪመጣ አናቆመውም፡፡

ፍሬውና በረከቱ ደስ ቢያሰኝም የምጥ ጸሎት ህመም አለው፡፡ለምሳሌ ነቢዩ ከባድና አስደንጋጭ መንፈሳዊ መልእክት ሰምቶ የጸለየው የምጥ ጸሎት ያስደንቀኛል፡፡እርሱም ኢሳ 21፡8 ላይ ይገኛል፡-‹‹…ስለዚህ ወገቤ ህመም ተሞላ እንደምትወልድ ሴት ምጥ ያዘኝ፤ከህመሜ የተነሳ አላይም፡፡ልቤ ተንበደበደ ድንጋጤ አስፈራኝ ተስፋ ያደረግሁትመ ድንግዝግዝታ መንቀጥቀጥ ሆነብኝ፡፡ ››ብሎ ይገልጸዋል፡፡የሚገርም ጸሎት ነው፡፡

ብዙ ጊዜ ሰዎች እንዲህ አይነትን ጸሎት ሲጸልዩ በጉልበታቸው ተንበርክከው ልክ እንደምትወልድ ሴት እያማጡ እየቃተቱ ለብዙ ሰአታት ይጸልያሉ፡፡እንዲህ አይነት ጸሎት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጠለቀ መንገድ በመዋሀድ የሚጸለይ ጸሎት ስለሆነ ብዙ ድንቅ ነገሮችን እናይበታለን፡፡

ለብዙ ለተለያዩ ጉዳዮች ይህንን ጸሎት ልንጸልይ እንችላለን ለምሳሌ ለነፍሶች መዳን፣ለቤ/ክ ማደግ፣ከተለያዩ አደገኛ ሁኔታዎች ለማምለጥ ፣ከምንታገልባቸው ሀጢያቶች ለመውጣት ወዘተ፡፡

ከእየሱስ ቀጥሎ እንደሀዋርያው ጳውሎስ ለቤ/ክ መወለድና ማደግ በእኩል ሁኔታ ያማጠ ሰው በምድር ላይ ያለ አይመስለኝም፡፡ጳውሎስ ገላ 4፡19 ላይ ስለዚህ አይነት ጸሎቱ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-‹‹ልጆቼ ሆይ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሰል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል፡፡ ››አያስቀናም! ራሱን የካደና የክርስቶስ ልብ የነበረው ሰው ነበር፡፡በዚህ አይነት ጸሎት ወሎ የሚያድር የነበረ ሰው ይመስለኛል፡፡ድንቅ አገልግሎት!እባክህ ጌታ ሆይ በእንደዚህ አይነት ጸሎት ባርከን!

እራሳችንን ለዚህ ጸሎት በሰጠንበት ልክ ይህ አይነት ጸሎት እየሰፋና እየጠለቀ ማቆሚያ ወደሌለው መንፈሳዊ ልምምድ ወስጥ ስለምንገባ ለብዙ ሰዎች በረከት እንሆናለን፡፡

ዮሀንስ 16፡20-22 ላይ ያለው ቃል እነዚያ 120 ክርስትያኖች እየሱስ ካረገ በኋላ በሰገነት(upper room) ላይ ወጥተው ስላከናወኑት የጸሎት ምጥ የተነገረ ትንቢታዊ ቃል እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡እንዲህ ይላል፡-‹‹እናንተ ታለቅሳላችሁ መኞም(ከበድ ያለ ለቅሶ ነው) ታወጣላችሁ…እናንተም ታዝናላችሁ ነገር ግን ሀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል….እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ ነገር ግን እንደገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል…››

በላይኛው ሀሳብ ላይ መንፈስ ቅዱስ ያሳየኝን ኡደት(cycle) ላስቀምጥ ፡-

የምጥ ጸሎት----------›እርሱ የእንደገና አምላክ ነወና ያየናል ------------›ልባችንም ደስ ይለዋል(ደስ የሚለወን የእንግሊዝኛ መጽሀፍ ቅዱሶች ከማጠን ያለፈ ደስታ እንደሆነ ለመግለጥ exceeding joy ብለው ይገልጹታል)-------------------›ከጀመርነው ከፍ ወዳለ የምጥ ጸሎት ወስጥ እንገባለን---------›የእንደገና አምላክ ያየናል---------------›ይቀጥላል

የምናሳልፈው ጊዜ በጣም ከባድና የሚያልፍ እስኪመስል ሊያስምጠንና ሊያስለቅሰን ይችላል፡፡ነገር ግን የእንደገና አምላክ በጉብኝቱ ሲመጣ ሶስት ነገር ነው የሚሆነው፡-

- እርሱ እንደገና ያየናል
- እኛም በሚደሰስና ግር በሚይል ሚልኩ እናየዋለን
- ምስክርነታችንም ግሩምና ጠንካራ ይሆናል

እዚህ ዮሀንስ ላይ የተጠቀሰው ቃል መጨረሻ ላይ ያለው ተስፋ ነው የሚያስደንቀኝ እንዲህ ይላል፡- ‹‹ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም፡፡››እንግሊዝኛው እንዲህ ይለዋል <<no one rob you of that joy>>በቀጥታ ሲተረጎም ማንም ይህንን ደስታ ሊዘርፋችሁ ወይም ሊገፋችሁ አይችልም ማለቱ ነው፡፡ለምን ማላችሁ እውነተኛ፣ሀይለኛ፣የጠለቀ፣በመንፈስ የጋየና ከወስጥ ከጥልቁ የተቀዳ ደስታ ስለሆነ ነው፡፡

ጌታ ሆይ በእንደዚህ አይነት ጸሎት ባርከን!

የሚልእክቱ አዘጋጅ በቀለ በላቸው(ዶ/ር) ስሆን የምኖረወም በሜሪላንድ ጌትስበርግ አካባቢ ነው፡፡በስነ-ጽሁፍና መጽሀፍ ቅዱስን በማስተማር ጌታን አገልግላለሁና ከኔ ጋር ለማስራት የምታስቡና በጽሁፌ ላይ አስተያየት ማስጠት ለምትፈልጉ በሚቀጥለው አድራሻዬ ልታገኙኝ ትችላላችሁ:-

Phone number: 240-330-5004/2405079148

Email address:beke_abay@yahoo.com